## ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምለሳ በጣም አስፈላጊ ነገሮች

(አርብ—የመጀመሪያ የማለዳ ክፍለ ጊዜ)

መልእክት አንድ

## ይህን ዘመን የሚያጠናቅቀውን አዲስ መነቃቃት ለማምጣት ከጌታ ጋር መተባበር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ዕንባ. 3፡2፤ ሐዋ. 26፡19፣ 22፤ ማቴ. 14፡19፣ 22-23፤ ፊልጵ. 1፡19-22፣ 25፤ ዮሐ. 21፡15-17

**I. በእግዚአብሔር ምርጦች መካከል መነቃቃትን መፈለግ ሁልጊዜም ነበር—ዕንባ. 3፡2፤ ሆሴ. 6፡2፤ ሮሜ 8፡20-22፤ መዝ. 119፡25፣ 50፣ 107፣ 154፤ ዮሐ. 6፡57፣ 63፤ 2 ቆሮ. 3፡3፣ 6።**

**II. በእግዚአብሔር ወደ ተሰጠን ወደ መለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ—ወደ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መገለጥ (1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 1 ቆሮ. 9፡17፤ ሐዋ. 26፡19፣ 22)—በመድረስ ወደ አዲስ መነቃቃት ውስጥ መግባት እንችላለን፤ ሰውን በመፍጠሩ እና የተመረጡ ሕዝቡን በማደቡ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ዓላማ በተመለከተ ለታላቁ ጥያቄ ታላቁ መልስ ይህ ነው (ዘፍ. 1፡26፤ ኢዮ. 10፡13፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡9)፦**

ሀ. በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የተሰወረው ምሥጢር የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ነው (1፡10፤ 3፡9፤ 1 ጢሞ. 1፡4)፣ ይህም በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለሚጠናቀቀው (ራእ. 21፡2—22፡5) ለእግዚአብሔር ሙላት፣ ለእግዚአብሔር መገለጥ (ኤፌ. 1፡22-23) ሕይወታዊ አካል፣ አዲሱ ሰው የሆነችው የክርስቶስ አካል ለመሆን (2፡15-16) እንደ የእርሱ ብዜቶች ከእርሱ ጋር አንድ አይነት ይሆኑ ዘንድ (ሮሜ 8፡29፤ 1 ዮሐ. 3፡2) ሕይወታቸው እና ባህሪያቸው ለመሆን ወደ መረጣቸው ሕዝቡ በመለኮታዊው ሥላሴ እንደ አብ በወልድ ውስጥ በመንፈስ ራሱን ለማደል ከልቡ መሻት ጋር የሆነው የእግዚአብሔር ውጥን ነው።

ለ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ለክርስቶስ አካል መፍራት እና መገንባት ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት እና በባህሪ ሰው እግዚአብሔር መሆን ይችል ዘንድ እግዚአብሔር ሰው መሆኑ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጠ-ነገር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ "ሳጥን" ውስጥ ያለው "አልማዝ"፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ነው—ዘፍ. 1፡26፤ ዮሐ. 12፡24፤ ሮሜ 8፡29፦

1. በተሠግዎ በኩል በሰው ስብዕና ውስጥ በመሳተፍ እግዚአብሔር ሰው ሆነ፤ በመለወጥ በኩል በእግዚአብሔር መለኮትነት ውስጥ በመሳተፍ ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት እና በባህሪ ሰው እግዚአብሔር ይሆናል—ዮሐ. 1፡14፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ቆላ. 3፡4፤ 2 ጴጥ. 1፡4፤ ፊልጵ. 2፡5፤ ሮሜ 8፡29፤ ዕብ. 2፡10፤ ኤፌ. 1፡5፤ ሮሜ 8፡19፤ 1 ዮሐ. 3፡2፤ ዮሐ. 1፡12-13።
2. ይህ የመለኮት-የስብዕና ፍቅር የመላው መጽሐፍ ቅዱስ ርዕሰ ጉዳይ፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ይዘት እና የመላው አጽናፍ-ዓለም ምሥጢር ነው—መኃ. 1፡1፤ 6፡13፤ ተዛ. ዕንባ. 1፡1፤ 2፡4፤ ሮሜ 1፡17፦
   ሀ. ክርስቶስ መለኮትም ሰውም ነው፤ የተለወጠችው አፍቃሪው ደግሞ ሰውም መለኮትም ናት፤ በሕይወት እና በባህሪ አንድ አይነት፣ እርስ በእርሳቸው ሙሉ በሙሉ እና ፍጹም የሚጣጣሙ ናቸው።
   ለ. ባል ለመሆን የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ እና ሙሽራይቱ ለመሆን የተለወጠው ሦስት-ክፍል ያለው ሰው አንድ ጥንድ፣ ብዙዎች የተካተቱበት፣ ታላቅ አምላክ-ሰው ለመሆን ነው—ራእ. 21፡2፣ 9፤ 22፡17።

ሐ. የእግዚአብሔር እና የጌታ ምለሳ ማዕከላዊው መገለጥ የክርስቶስ አካል የምትሆነውን (ኤፌ. 4፡15-16) እና አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን የምታጠናቅቀውን (ራእ. 21፡2፣ 9፤ 22፡17፤ ተዛ. ዘፍ. 2፡22፤ ዮሐ. 19፡34) ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት (ማቴ. 16፡18) እግዚአብሔር *ሥጋ መሆኑ* (ዮሐ. 1፡1፣ 14)፣ *ሥጋ* ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ መሆኑ (1 ቆሮ. 15፡45) እና ሕይወት-የሚሰጠው መንፈስ ሰባት እጥፍ ያየለ መንፈስ መሆኑ (ራእ. 1፡4፤ 3፡1፤ 4፡5፤ 5፡6) ነው።

መ. እግዚአብሔር እና ሰው አንድ አካል ይሆናሉ፣ ያም አንድ አካል የመላው መጽሐፍ ቅዱስ መደምደሚያ የሆነችውን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን የሚያጠናቅቀው የመለኮት ከስብዕና ጋር መዋሐድ ነው—ራእ. 21፡3፣ 22፣ 2፣ 9፤ ተዛ. ዘሌ. 2፡4-5፤ መዝ. 92፡10።

ሠ. "በምድር ሁሉ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ውስጥ ያሉ ቅዱሳን፣ በተለይ አብሮ-ሠራተኞች እና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፣ ይህን መገለጥ እንደሚያዩ ከዚያም እግዚአብሔር አዲስ መነቃቃትን—ፈጽሞ በታሪክ ተዘግቦ የማያውቅ መነቃቃትን—ይሰጠን ዘንድ ለመጸለይ እንደሚነሡ ተስፋ አደርጋለሁ"—*Life-study of 1 and 2 Chronicles,* ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 15 የተወሰደ።

**III. የክርስቶስ አካል እውነታ የሆነውን የአምላክ-ሰው ሕይወትን መኖር በተግባር ከተለማመድን፣ ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ ብዙዎች የተካተቱበት ሞዴል፣ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖር ሞዴል ይገነባል፤ ይህ ሞዴል ጌታን መልሶ ለማምጣት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛው መነቃቃት ይሆናል—መዝ. 48፡2 እና የግርጌ ማስታወሻ 1፤ ራእ. 3፡12፣ 21፡-**

*ሀ.* እግዚአብሔር በመለኮታዊው መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ በኩል በዚህ መገለጥ መሠረት የሆነ ሕይወት ለመኖር ብዙዎች የተካተቱበት ሕዝብ በጸጋው እንዲነሣ ይፈልጋል፤ መነቃቃት ያየነው ራእይ ተግባራዊ ልምምድ፣ ተግባራዊነት ነው።

ለ. የክርስቶስ ተከታዮች (ማቴ. 5፡1፤ 28፡19) እንደ የአምላክ-ሰው ሞዴል—በሰብዕናው ራሱን በመካድ እግዚአብሔርን በኖረው (ዮሐ. 5፡19፣ 30)፣ ሰውን በተመለከተ የነበራቸውን ጽንሰ-ሃሳብ ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ በለወጠው (ፊልጵ. 3፡10፤ 1፡21)—በምድር ላይ በነበረው የክርስቶስ የሰብዕና ኑሮ በኩል ሰለጠኑ።

ሐ. ሕይወታችን የመጀመሪያው አምላክ ሰው የሆነው የክርስቶስ ሕይወት ሞዴል ቅጂ፣ ርቢ መሆን አለበት—1 ጴጥ. 2፡21፤ ማቴ. 11፡28-29፤ ኤፌ. 4፡20-21፤ ዮሐ. 17፡4፤ 5፡17፤ ፊልጵ. 1፡19-22፣ 25።

መ. ወደ ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ የተተነፈሰው የሕይወት እና የእውነታ መንፈስ ለሦስት ዓመት ተኩል ከጌታ ጋር በነበሩበት ጊዜ ከጌታ ወደተመለከቱት ነገር እውነታ ሁሉ ይመራቸዋል—ዮሐ. 16፡13፤ 20፡22፡-

1. በመጀመሪያው አምላክ-ሰው አገልግሎት ጅማሬ፣ በሥጋው መሠረት (በሰብዕናው—1፡14፤ ሮሜ 1፡3፤ 8፡3) ለመሞት እና ለመቀበር እንጂ ለምንም እንደማይጠቅም በመገንዘብ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም ተጠመቀ—ማቴ. 3፡15-17።
2. አምስት ሺውን ሕዝብ በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ በመገበበት ተዓምር ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ እንዲማሩ አሰለጠናቸው (11፡29)፤ አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ለመባረክ "ወደ ሰማይ አሻቅቦ" ማየቱ (14፡19) የበረከት ምንጩ እርሱ፣ የተላከው ሳይሆን አብ፣ ላኪው እንደሆነ መገንዘቡን ያመለክታል (ዮሐ. 10፡30፤ 5፡19፣ 30፤ 7፡6፣ 8፣ 18)።
3. ጌታ በተዓምሩ ጉዳይ ላይ ከሕዝቡ ጋር አልቆየም ነገር ግን በተራራው ላይ በጸሎት በግሉ ከአብ ጋር ለመሆን ትቷቸው ሄደ—ማቴ. 14፡22-23፤ ሉቃ. 6፡12።
4. ጌታ ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ በመኖር (ሐዋ. 10፡38፤ ዮሐ. 8፡29፤ 16፡32) እግዚአብሔርን የመገናኘትን (ማር. 1፡35፤ ሉቃ. 5፡16፤ 6፡12፤ 9፡28፤ ዕብ. 7፡25)፣ እና ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ኢዮቤልዩ ውስጥ ለማምጣት እግዚአብሔርን ወደ ውስጣቸው በማገልገል ሕዝቡን የመገናኘትን ሕይወት ኖረ (ሉቃ. 4፡18-19፤ ዕብ. 8፡2፤ ተዛ. ዘፍ. 14፡18፤ ሐዋ. 6፡4)።
5. የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ሰይጣን በእርሱ ላይ ምንም ያልነበረው ሰው ነበር (በማንኛውም ነገር ምንም ስፍራ፣ ምንም እድል፣ ምንም ተስፋ፣ ምንም የመሆን እድል የሌለው)—ዮሐ. 14፡30፤ ተዛ. ቁ. 20፤ 2 ቆሮ. 12፡2፤ ቆላ. 1፡27፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ ዮሐ. 3፡6፤ 4፡23-24፤ 1 ዮሐ. 5፡4፣ 18።

ሠ. በጌታ ሞዴል መሠረት የአምላክ-ሰው ሕይወትን ለመኖር ብቸኛው መንገድ መላው ማንነታችንን በተዋሐደው መንፈስ ላይ ማድረግ፣ መመላለስ፣ መኖር እና ማንነታችንን በተዋሐደው መንፈስ መሠረት ማድረግ ነው—ሮሜ 8፡2፣ 4፣ 10፣ 6፣ 11፣ 16፤ 1 ቆሮ. 6፡17፤ ሮሜ 10፡12፤ ገላ. 5፡25፤ ኤፌ. 6፡17-18፤ 1 ተሰ. 5፡16-20፤ 1 ጢሞ. 4፡6-7፤ 2 ጢሞ. 1፡6-7።

ረ. "ሁላችንም የአምላክ-ሰው ሕይወት መኖር እንደምንፈልግ ማወጅ አለብን። በመጨረሻም፣ አምላክ-ሰዎቹ አሸናፊዎች፣ ድል-ነሺዎች፣ በኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ ጽዮን ይሆናሉ። ይህ ፈጽሞ በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ መነቃቃትን ያመጣል፣ ይህም ይህንን ዘመን ከፍጻሜ ያደርሳል"—*Life-study of 1 and 2 Chronicles* ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 28 የተወሰደ)።

**IV. የእግዚአብሔርን መንጋ፣ የክርስቶስን አካል የምታመጣውን ቤተ ክርስቲያንን ለመንከባከብ ጠቦቶቹን ለመመገብ እና በጎቹን በእረኝነት ለመንከባከብ በክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት በመሳተፍ ወደ አዲስ መነቃቃት ውስጥ መግባት እንችላለን፤ ይህ ሐዋርያዊውን አገልግሎት ከክርስቶስ ሰማያዊ አገልግሎት ጋር ለማካተት ነው—ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ጴጥ. 2፡25፤ 5፡1-4፤ ዕብ. 13፡20-21፤ ራእ. 1፡12-13፡-**

*ሀ.* ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መከናወን ሰዎችን ጌታ ኢየሱስ በአገልግሎቱ በነበረው ምሳሌ መሠረት በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—ማቴ. 9፡36፤ ዮሐ. 10፡11፤ ዕብ. 13፡20፤ 1 ጴጥ. 5፡4፡-

1. በሙሉ ማዳኑ ውስጥ ያለው የመላው የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ይዘት ክርስቶስ እንደ የሰው ልጅ በሞቱ በኩል ፍትሃዊ ቤዛነቱን በመፈጸም እኛን ከኃጢአት በመዋጀት ማስደሰቱ (1 ጢሞ. 1፡15፤ ኤፌ. 1፡7) እና

ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ልጅ በትንሣኤው ሕይወታዊ ማዳኑን በማከናወን መለኮታዊውን ሕይወት አብዝቶ ወደ ውስጣችን ለማካፈል እኛን መመገቡ ነው (ዮሐ. 10፡10፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ኤፌ. 5፡29)።

2. የአብ አፍቃሪ እና ይቅር ባይ ልብ እና የአዳኙ በእረኝነት የሚንከባከብ እና የሚፈልግ መንፈስ የሌለን መሆናችን ለመካንነታችን ምክንያት ናቸው—ሉቃ. 15፡1-24።
3. በኢየሱስ ስብዕና ሰዎችን ማስደሰት (ደስ እንዲላቸው ማድረግ እና ደስተኛ እና ምቾት እንዲሰማቸው ማድረግ) ያስፈልገናል (ማቴ. 9፡10፤ ሉቃ. 7፡34)፤ በክርስቶስ መለኮትነት ሰዎችን መመገብ (ሁሉን-ባካተተው ክርስቶስ በአገልግሎቱ ሦስት ደረጃዎች መመገብ) ያስፈልገናል—ማቴ. 24፡45-47።
4. ክርስቶስ አንዲት አመንዝራ ሴትን እንደ የሕይወት ውኃ ወንዝ በሚፈስሰው በሦስታንዱ አምላክ ለመመገብ የሚጠጣ ነገር እንድትሰጠው በመጠየቅ እርሷን በማስደሰት ለማግኘት፣ ሆነ ብሎ ሩቅ መንገድ በመዞር ወደ ሲካር ለመሄድ በሰማርያ ማለፍ ግድ ሆነበት—ዮሐ. 4፡3-14፤ ራእ. 22፡1።
5. ኃጢአት የሌለበት ማንነት የሆነው እርሱ አመንዝራይቱን ሴት አልኮነናትም ነገር ግን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ስለ ኃጢአቶቿ ይቅርታ እና ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ከኃጢአቶቿ ነጻ ስለመውጣቷ አስደሰታት (ዮሐ. 8፡1-11፣ 32፣ 36)፤ በተጨማሪም በመስቀሉ በኩል በክርስቶስ የዳነው የመጀመሪያው ሰው ሞት የተፈረደበት ወንበዴ መሆኑ ትርጉም ያዘለ ነው (ሉቃ. 23፡42-43)።
6. ጌታ የቀራጮች አለቃ የሆነን አንድን ሰው ለመጎብኘት እና ለማግኘት ወደ ኢያሪኮ ሄደ፣ ስብከቱም በእረኝነት መንከባከቡ ነበር (19፡1-10)፤ በተጨማሪም በልጆቻቸው ላይ እጆቹን በመጫን ወላጆቻቸውን አስደሰታቸው (ማቴ. 19፡13-15)።

ለ. የእግዚአብሔርን መንጋ ለመንከባከብ እንደ የምታጠባ እናት እና አጥብቆ እንደሚመክር አባት ቅዱሳንን በእረኝነት በተንከባከበው በሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌ መሠረት ሰዎችን በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—1 ተሰ. 2፡7-8፣ 11-12፤ 1 ጢሞ. 1፡16፤ ሐዋ. 20፡28፦

1. ጳውሎስ በኤፌሶን የነበሩ ቅዱሳንን "በጉባኤም በየቤታቸውም" በማስተማር (ቁ. 20) እና የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ በመንገር (ቁ. 27) ለሦስት ዓመታት በእንባ እያንዳንዱን ቅዱሳን በመገሠጽ (ቁ. 31፣ 19) በእረኝነት ተንከባከባቸው።
2. ጳውሎስ ለአማኞች ጥልቅ ግድ መሰኘት ነበረው (2 ቆሮ. 7፡2-7፤ ፊልሞና 7፣ 12)፣ እነርሱን ለማግኘት ወደ ደካማዎቹ ደረጃ ወረደ (2 ቆሮ. 7፡2-7፤ 11፡28-29፤ 1 ቆሮ. 9፡22፤ ተዛ. ማቴ. 12፡20)።
3. ስለቅዱሳን ንብረቱን የሚያመለክተውን የነበረውን ሁሉ ለመስጠት እና ማንነቱን የሚያመለክተውን የሆነውን ነገር ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር (2 ቆሮ. 12፡15)፤ እርሱ የመጠጥ መሥዋዕት ነበር፣ ሌሎች ክርስቶስን ይደሰቱ ዘንድ ራሱን መሥዋዕት በማድረግ የወይን ጠጅ ከሚያፈልቀው ክርስቶስ ጋር አንድ ነበር (ፊልጵ. 2፡17፤ መሣ. 9፡13፤ ኤፌ. 3፡2)።
4. ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለማክበር በመንፈስ ተመላለሰ ይህም ሰውን ለማክበር መንፈስን ማገልገል ይችል ዘንድ ነው—2 ቆሮ. 3፡3፣ 6፣ 8፤ ገላ. 5፡16፣ 25፤ መሣ. 9፡9።
5. ጳውሎስ በትምህርቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ለማሳደግ ቤት፣ እነርሱን ለመፈወስ እና ለመመለስ ሆስፒታል እንዲሁም እነርሱን ለማስተማር እና ለማነጽ ትምህርት ቤት እንደሆነች ጠቁሟል—ኤፌ. 2፡19፤ 1 ተሰ. 5፡14፤ 1 ቆሮ. 14፡31።
6. [ጳውሎስ] ለክርስቶስ አካል ግንባታ ማንኛውንም ነገር ለመሆናችን እና ማንኛውንም ነገር ለማድረጋችን ፍቅር የላቀው መንገድ መሆኑን ገልጿል—8፡1፤ 12፡31፤ 13፡4-8፤ ኤፌ. 1፡4፤ 3፡17፤ 4፡2፣ 15-16፤ 5፡2፤ 6፡24፤ ራእ. 2፡4-5፤ ቆላ. 1፡18፤ 1 ተሰ. 1፡3።

ሐ. "ይህን በእረኝነት የመንከባከብ ሸክምን በመቀበላችን በመካከላችን እውነተኛ መነቃቃት ይኖራል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በክርስቶስ ድንቅ የእረኝነት እንክብካቤ ውስጥ ለመሳተፍ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ይህን ትምህርት ከተቀበሉ፣ በምለሳው ትልቅ መነቃቃት ይኖራል"—*The Collected Works of Witness Lee, 1994-1997,* vol. 5, "The Vital Groups," ከሚለው መጽሐፍ፣ ከገጽ 92 የተወሰደ።

*© 2021 Living Stream Ministry*